
Addis
POWERHOUSE



tila

A Digital Safety & Resilience Toolkit

for Women on the Frontlines to Combat Technology-Facilitated Gender-Based Violence


tila

Contents

What is Technology-Facilitated Gender-Based Violence (TFGBV)? 8

How TFGBV Impacts You: Recognizing the Warning Signs 11

What can YOU Do When TFGBV Happens 13

Digital well-being: Care as a resistance 17

Online Safety on the Move - Treat Public Wi Fi as High Risk. 19

Digital Solidarity: We are each other's security. 21

ማውጫ

በቴክኖሎጂ የታገዘ ጾታዊ ጥቃት (TFGBV) ምንድን ነው? 28

በቴክኖሎጂ የታገዘ በጾታ ላይ የተመሰረተ ጥቃት የሚያሳድረው ተጽዕኖ፡- የማስጠንቀቂያ ምልክቶችን መለየት 31

ቴክኖሎጂተኮር የፆታ ጥቃት ሲያጋጥምሽ ምን ማድረግ ትችያለሽ? 34

የዲጂታል ደህንነት፡- 37

በጉዞ ላይ የሚደረጉ የደህንነት ጥንቃቄዎች – የህዝብ ዋይፋይን እንደ ከፍተኛ ስጋት ተመልከቺ 40

ዲጂታል አጋርነት፡- እርስ በርሳችን የደህንነት ጋሻዎች ነን 42

Baafata

Haleellaan Saalaa Tekinooloojiidhaan Deggeramee Raawwatu (TFGBV) Maali? 48

Akka itti TFGBVn dhiibbaa sirratti uumu: Mallattoolee akeekkachiisummaa adda baasuu. 51

Yeroo TFGBV Si Mudatu Maal Gochuu Dandeessa? 54

Fayyaa Dijitaalaa : of Eeggannoo akka mormiitti. 57

Nageenya Interneetaa Yeroo Sochii 60

Nageenya waloo Dijitaalaa (Digital Solidarity): Nuti eegdota walii keenyaati. 61

ማውጫ

ብቴክኖሎጂ ዝተሓገዘ ፆታ መሰረት ዝገበረ ጥቓዓት(TFGBV) እንታይ እዩ? 68

TFGBV ብኸመይ ይፀልው፡ ዘጠንቅቀቕ ምልክታት ምልላይ 71

TFGBV እንተጋትም እንታይ ክንገብር ንኽእል 73

ዲጂታላዊ ድሕንነት : ክንክን ከም መስረሕ ቃልሲ 76

ድሕነት ኦንላይ ምትግባር - ኦንላይን ድሕነት - ሓበራዊ ዋይፋይ ከም ልዑል ሓደጋ ምርኣይ 78

ዲጂታላዊ ሓድነት: ንንሕድሕድና ዋሕስ ኢና 80

About Addis Powerhouse

Addis Powerhouse (APH) is a young women-led feminist knowledge production and advocacy hub dedicated to equipping young women in Ethiopia with the research, digital literacy, and media platforms needed to challenge socio-political exclusion and gender-based violence (GBV). Our organisation was founded in 2020 during the COVID-19 lockdown, a period when gendered disparities in socioeconomic and political systems were visibly exacerbating, and social and professional lives were rapidly shifting online. During this transition, we witnessed how biased gender data, rampant spread of misinformation, and GBV further marginalized women on and offline. These emerging threats have inspired us to employ strategic, research-oriented, rights-based advocacy, transforming marginalized voices into knowledge, movement and systemic impact. Since our inception, the APH team has produced multiple research, campaigns, and storytelling documentaries and the first feminist podcast in Ethiopia, amplifying women's voices at the national level.

Foreword

When we founded Addis Powerhouse, we knew that to close the gender gap, we had to protect the young women leading the way. In Ethiopia's rapidly shrinking civic space, where surveillance, disinformation, and coordinated attacks have become common tools of silencing, our safety is no longer optional - it has become our prerequisite for activism.

ጥላ (TILA) toolkit, named after the Amharic word for "umbrella," represents a protective shield for women on the frontlines navigating the digital harassment, threats, and attacks that aims to silence their work. It is one product within a package of resources we have prepared to provide you with practical guidance to recognize digital risks, protect yourself, and continue your advocacy safely, strengthening your courage and resilience along the way.

We created **TILA** so that you don't have to choose between your safety and your voice.

We believe our movement is only as strong as the women who lead it. Use these resources to guard your digital borders and to stay loud!

The APH Team
January 2026

What is Technology-Facilitated Gender-Based Violence (TFGBV)?

According to the definition by UNFPA, "Technology-facilitated gender-based violence, or TFGBV, is an act of violence perpetrated by one or more individuals that is committed, assisted, aggravated, and amplified in part or fully by the use of information and communication technologies or digital media, against a person based on their gender." 1

Further analysis by Collaboration on International ICT Policy for East and Southern Africa (CIPESA) highlights that women at heightened risk of online violence include those with a public profile. This includes women journalists, women human rights defenders, women's rights activists, young women and girls, and women with intersecting identities who face compounded discrimination and targeted attacks.2

1 *Brochure: What is technology-facilitated gender-based violence?* published by **UNFPA,** March 2023.

2 Collaboration on International ICT Policy for East and Southern Africa (CIPESA), research on online violence against women in Africa.



Forms of TFGBV

- **Online Harassment:** Constant, aggressive messages meant to intimidate and exhaust you.
- **Cyberstalking:** Using digital tools to track your location or monitor your movements in real time.
- **Image-Based Abuse:** Weaponizing images, including AI-generated deepfakes to shame or objectify you.
- **Doxxing:** Leaking your private details, like your home address or phone number, to invite physical harm.
- **Digital Sexual Abuse:** Using messaging apps or social sites to harass, coerce, or procure assault.
- **Luring:** Tricking victims into dangerous physical situations through digital deception.
- **Hacking:** Illegally breaking into your accounts to steal data, ruin your reputation, or disrupt your organization.
- **Hate Speech:** Using discriminatory language to attack you based on your identity

Common forms of TFGBV

In Ethiopia, TFGBV violence is often used to silence women by weaponizing social, cultural, and religious norms. These attacks are not "just online"; they are real-world threats designed to discredit you and stop your advocacy.

Tactic	Description
Online Harassment & Hate Speech	Using gendered insults, body-shaming, or religious language to call you "immoral" or "anti-culture." It is an attempt to shame you into silence.
Threats of Sexual Violence & Death	Receiving explicit messages threatening rape, acid attacks, or killing. Attackers may also threaten your children or family members to force you to comply.
Doxxing	Exposing your private details, like your home address, phone number, or workplace, without your consent. This is done to invite physical stalking or harm.
Non-Consensual Image Sharing	Distributing or threatening to release private or intimate images to humiliate you. This includes using AI to create fake sexualized images (Deepfakes).
Impersonation (Fake Accounts)	Creating profiles that look like you to spread ethnic hatred or "anti-religious" views. The goal is to provoke a violent social or political reaction against you.
Coordinated Disinformation	Organized groups work together to label you a "Satanist," "lesbian," or "foreign agent." They repeat these lies across TikTok and Telegram until people believe they are true.
Hacking & Surveillance	Breaking into your accounts or stealing your phone to read your private messages. It also involves tracking your calls and emails to monitor your activism.

How TFGBV Impacts You: Recognizing the Warning Signs

Technology-Facilitated Gender-Based Violence (TFGBV) targets women activists, journalists, and defenders both personally and professionally. It is designed to undermine your mental health, disrupt your work, and create real-world safety risks. Recognizing these impacts early helps you take the necessary protective measures.

Impact of Online Harassment

Impact Area	How it Feels
Psychological Harm	Experiencing persistent anxiety, fear, trauma, or total exhaustion (burnout) from constant online harassment.
Self-Censorship	Feeling forced to withdraw from online spaces, deleting social media, or staying quiet to avoid more attacks.
Reputational Damage	A loss of trust or professional credibility due to lies, which can harm your career and professional relationships.
Isolation	Distancing yourself from your friends, colleagues, and support networks out of fear or shame.
Offline Danger	Online abuse escalating into real-world stalking, physical attacks, or threats against your home and children.

Example: When a Threat Moves Offline

In Ethiopia, digital violence often follows a predictable path of escalation. Understanding this pattern can help you identify when you are in physical danger.

A feminist activist in Ethiopia, who often posts about women's rights online, starts receiving violent comments. Here is how threats can escalate:

1. **Public Targeting:** Harassers begin with violent comments on your posts.
2. **Narrative Warfare:** Fake accounts spread lies, calling you "anti-religion," "lesbian," or a "foreign agent" to trigger a community backlash.
3. **The Privacy Breach:** A harasser posts a photo of your home or comments on your daily commute route.
4. **Family Intimidation:** You receive messages mentioning your children or relatives, warning you to "stay quiet".
5. **Direct Contact:** Harassment crosses platforms, and you start receiving anonymous phone calls repeating the threats you saw online.

Important Alert: If you recognize these signs, the online threats are escalating into physical and offline danger.

Disproportionate burden: Women are often expected to endure harassment silently, making the impact heavier and less visible.

Remember, at this stage, your physical safety must become the immediate priority!

What can YOU Do When TFGBV Happens

1

Save the Proof (Document Everything)

Do not delete the hateful messages right away. You need them as "evidence" if you go to a lawyer or the police.

- **How to do it:** Take pictures (screenshots) of the messages, the person's profile, and the hateful comments.
- **What to include:** Make sure your picture shows the **date and time** it happened. Save the links (URLs) to the profiles or posts so they can be tracked even if the person changes their name.

2

Protect Your Accounts

If you are under attack, you must secure your accounts immediately.

- **The 12-Character Password:** Change your password to something very long, at least 12 characters. Use a mix of big and small letters, numbers, and symbols like (#, !, or ?). Do not use your name or birthday.

A strong password:

- Must have more than 12 characters, which includes letters (CAPS and Lower case), symbols, and numbers
- It must be Unique and different for every account
- It should never be based on personal details or easily guessed by people who know you.

Enable Two-Factor Authentication (2FA): This is your best defense. It adds a "second lock" to your account. Even if a hacker has your password, they can't get in without a special code sent to your phone.

How to enable 2FA

1. Go to your account's security settings.
2. Look for Two-Factor Authentication or Login Verification and turn it on.
3. Choose a method:
4. SMS: Codes are sent to your phone.
5. Authentication app: Use apps like Google Authenticator or Microsoft Authenticator
6. Enter the code each time you log in after your password.

3

Silence the Perpetrators (Report and Block)

You have the right to block anyone trying to hurt you.

- **Block Them:** Use the "Block" button on the person's profile so they can never message you or see your posts again.
- **Report to the Platform:** Use the "Report" button to tell Facebook, TikTok, or Telegram that this person is harassing you. It is the platform's job to protect you.

4

Don't Face the Mob Alone (Seek Support)

Perpetrators want you to feel isolated. Reach out to others to break that silence.

- **Tell Your Network:** Talk to trusted friends, family, or your professional network.
- **Ask for "Digital Solidarity":** Ask your friends to help report the abusive account. When many people report at once, the platform is more likely to take the account down.

5

Take a Tactical Break

Taking a break is a sign of strength, not a sign of giving up.

It is okay to stop posting or hide your profile for a few days while you deal with the threats. Taking a break is not giving up!

Use the Legal Shield

Online harassment is a crime in Ethiopia.

- **Computer Crime Law Proclamation:** This law (No. 958/2016) protects you from online threats and identity theft.
- **Hate Speech and Disinformation Proclamation:** This law (No. 1185/2020) protects you from gendered hate speech.
- **Talk to Experts:** To assist you in filing a report, contact your organization's security team, a lawyer, or a human rights organization working on digital rights.



Digital well-being: Care as a resistance

Digital wellbeing isn't just about "screen time", it's about making sure the internet doesn't steal your peace or your purpose. When you are under attack, your mind is the first target.

Recognize the "Digital Weight"

Online violence is designed to make you feel heavy. Watch for these red flags:

- **Hyper-vigilance:** Constantly checking your phone for new attacks or "waiting for the next bomb to drop."
- **The Isolation Trap:** Feeling like you can't tell your family or friends because they'll just tell you to "get offline."
- **Body Reactions:** Feeling your heart race or your stomach churn every time a notification pings.

Protective Measures for Your Mind

Use these "Digital Boundaries" to keep the noise out:

- **Separate Your Spaces:** If possible, use a different social media account for your work and a different one to connect with family and friends. It preserves emotional energy by containing harm to one space.
- **Filtered Content:** Use tools to hide specific words or slurs from your comments.

On Youtube, X and Instagram: Go to "Privacy Settings" > "Muted Words" and add the slurs or labels (like "foreign agent") used against you.

- **Curate Your Feed:** You are what you consume. Unfollow accounts that make you feel angry or small. Follow "Digital Safe Spaces" and other women who inspire you.
- **The "Sunset" Rule:** Stop checking your work accounts two hours before bed. Your brain needs time to "de-scramble" from the digital world to sleep.

Think of this as a "Digital Wellness" checkup. Set a reminder on your phone for the first day of every month to go through this list.

Habit	What to do	☐
Clear Your "Footprints"	Delete apps you haven't used in 3 months. Go to your phone's "App Permissions" and turn off access to your camera and location for apps that don't need them.	
Sweep Your Logins	Go to the "Security" tab on Facebook, Telegram, and Gmail. Look for "Logged-in Devices". If you see a phone or city you don't recognize, tap "Log Out" immediately.	☐
Software Polish	Check for updates on your phone and laptop. These updates are like "patches" that fix holes hackers use to get into your device.	☐
Check Your "Shield"	Open your VPN (like ProtonVPN) and make sure it's still working. Check if your Password Manager is backed up and that you still remember your Master Password.	☐
The Google Test	Search for your own name and phone number on Google. If you find your home address or private info (Doxxing), use the "Report" tool on the search result to ask Google to remove it.	☐

Online Safety on the Move - Treat Public Wi Fi as High Risk.

Using the internet in a cafe or airports can be risky because these networks are often unencrypted.

The Trap



Hackers can create a fake Wi-Fi network with a name like “Cafe_Free_WiFi” to trick you into connecting so they can see your traffic.

The Solution

Don’t connect if you don’t have to. Use your mobile data instead.

If you must connect: Turn on your **VPN** first. This creates a “secure tunnel” around your data.

Avoid sensitive tasks: Never log into your bank account or send private activist documents while on public Wi-Fi.

How to use a VPN:

1. Choose a trustworthy VPN (examples: ProtonVPN, Windscribe). Free or paid versions are available.
2. Download and install the VPN app on your device.
3. Open the app and select a server (choose your country or a nearby country).

Note: Turn the VPN on before using the internet.



Digital Solidarity: We are each other's security.

Digital solidarity means refusing to allow women to face online violence alone. Perpetrators gain power from our silence and often try to isolate their targets. For women on the frontlines, standing together reduces this isolation and shows that no one has to face these attacks by themselves.

During recent Gen Z-led movements, young activists across multiple countries used social media, messaging platforms, and online coordination tools to rapidly share information, support one another, and organize collective action. They amplified each other's messages, coordinated responses to digital repression, and created a sense of shared purpose that helped protect participants and spread awareness beyond their local contexts.

Whenever you see a sister being targeted by TFGBV, don't just scroll, take action!

Action	What you can do
Call Out the Abuse	Publicly speak out against the harassment or the perpetrators to show that this behavior is not acceptable.
Collective Reporting	Work with others to report the abusive content to the platform (Facebook, TikTok, etc.) all at once. This increases the chance of the content being removed.
Share Resources	Pass along safety tools, warnings, and guides like this one to help others protect themselves.
Amplify Her Voice	Share the victim's original message or work to ensure her voice is not drowned out by the noise of the attackers.
Rapid Response	Coordinate with your networks during a crisis to provide immediate support and share information quickly.

For women on the frontlines, Collective responses can increase safety by discouraging perpetrators, amplifying accurate information, and ensuring threats are seen and documented. By acting together, digital solidarity shifts power away from abusers and helps build collective resilience, allowing women to continue their work with greater confidence and support.

TFGBV is not normal, and women should not accept it as a consequence of being online. It is a human rights issue that can be confronted through collective action, protection, and solidarity. According to feminist theory, gendered violence is rooted in patriarchal power structures, and collectively resisting it is an act of feminist agency and empowerment.

Survival is resistance, Care is political!


አማርኛ

አዲስ ፓወር ሀውስ

አዲስ ፓወር ሀውስ በወጣት ሴቶች ተመስርታ በወጣት ሴቶች የምትመራ የፌሚኒስት ማዕከል ስትሆን፤ ዓላማዋም በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ወጣት ሴቶችን በምርምር፣ በዲጂታል ዓረዳድ ክህሎት እና በሚዲያ አማካኝነት በማብቃት በጾታ ላይ የተመሰረቱ ጥቃቶችን እንዲከላከሉ መርዳት ነው።

ድርጅቱ በ2020 (እ.ኤ.አ) የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ወቅት የተመሰረተ ሲሆን፣ ይኽ ወቅት በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ስርዓቶች ውስጥ ያለው የጾታ ልዩነት በግልጽ እየተባባሰ የመጣበት እንዲሁም ማህበራዊ እና ሙያዊ ዘይቤ በፍጥነት ወደ ኢንተርኔትን ተኮር (internet based) እየተቀየረ የነበረበት ወቅት ነበር።

በዚህ የሽግግር ወቅት፣ አድሏዊ የጾታ መረጃዎች፣ የሀሰት መረጃዎች እና በጾታ ላይ የተመሰረቱ ጥቃቶች በአውታረ መረብ (online) ሆነ ከአውታረ መረብ ውጭ (offline) በስፋት መሰራጨት እንዴት ሴቶችን ተጋላጭ እንዳደረጋቸው ተመልክተናል።

እነዚህ እየመጡ ያሉት ስጋቶች ስልታዊ፣ ምርምርን መሰረት ያደረጉ እና መብት ተኮር ስራዎችን (advocacy) እንድንጠቀም አነሳስተውናል፤ ይህም የተገለሉ ድምጾችን ወደ እውቀት፣ ወደ ንቅናቄ እና ወደ ስርአታዊ ለውጥ እንዲቀየሩ ለማድረግ ነው።

አዲስ ፓወር ሀውስ ከተመሰረተችበት ጊዜ ጀምሮ፣ በርካታ ምርምሮችን፣ ዘመቻዎችን እና የታሪክ ሰነድ ፊልሞችን እንዲሁም በኢትዮጵያ የመጀመሪያውን የፌሚኒስት ፖድካስት በማዘጋጀት የሴቶችን ድምጽ በሀገር አቀፍ ደረጃ እንዲሰማ አድርጋለች።

መቅድም

አዲስ ፓወር ሀውስን ስንመሰርት፣ የጾታ ልዩነትን ለማጥበብ ወጣት ሴት መሪዎችን ከተለያዩ ጥቃቶች መጠበቅ እንዳለብን ስለተረዳን ነበር። በኢትዮጵያ የሲቪክ ምህዳር ውስጥ፤ ክትትል፣ የሀሰት መረጃ እና የተቀነባበሩ ጥቃቶች ሴቶችን ዝም ለማሰኘት የተለመዱ መሣሪያዎች በመሆናቸው ደህንነታችን ምርጫችን ሳይሆን የእንቅስቃሴያችን አንድ አካል በማድረግ እየሰራን እንገኛለን።

ጥላ

የሚለው ስያሜ የተወሰደው "ጃንጥላ" ከሚለው የአማርኛ ቃል ሲሆን፣ ይህም በዲጂታል ዓለም ውስጥ ትንኮሳ እና ጥቃት ለሚሰነዘርባቸው ሴቶች እንደ መከላከያ ጋሻ ሆኖ እንዲያገለግል ታስቦ የተዘጋጀ ነው። ይህ መሣሪያ የዲጂታል ስጋቶችን ለመለየት፣ ራስን ለመጠበቅ እና እንቅስቃሴን በደህንነት ለመቀጠል የሚያስችል ተግባራዊ መመሪያ ይሰጣል።

ይህ መመርያ ለመስጠት ካዘጋጀናቸው የግብዓት ጥቅሎች አንዱ ሲሆን፤ የዲጂታል ስጋቶችን እንድትለዩ፣ ራስሽን እንድጠብቂ እና የንቅናቄ ስራሽን (advocacy) በደህንነት እንድትቀጥይ ፤እንዲሁም ጥንካሬሽን እና አቅምሽን አንድታጎለብቺ ያግዛል።

ንቅናቄያችን ጠንካራ የሚሆነው በሚመሩት ሴቶች ጥንካሬ ልክ እንደሆነ ስለምናምን፣በደህንነትሽ እና በድምጽሽ መካከል መምረጥ እንዳይኖርብሽ ጥላን አዘጅተናል።

የዲጂታል ወሰኖችሽን ለመጠበቅ እና ድምጽሽን ከፍ አድርጎሽ ለመቀጠል የጥላን ግብዓቶች ተጠቀሚ!

የአዲስ ፓወር ሀውስ ቡድን
ጃንዋሪ 2026/ጥር 2018

በቴክኖሎጂ የታገዘ ጾታዊ ጥቃት (TFGBV) ምንድን ነው?

የተባበሩት መንግስታት የህዝብ ፈንድ (UNFPA) ትርጓሜ እንደሚያስረዳው፣ "በቴክኖሎጂ የታገዘ መሰረተ ጾታ ጥቃት (TFGBV) ማለት በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ግለሰቦች አማካኝነት በመረጃ እና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂዎች ወይም በዲጂታል ሚዲያዎች በመታገዝ፣ በመደገፍ፣ በማባባስ ወይም በማስፋፋት በአንድ ሰው ላይ በጾታው ምክንያት የሚፈጸም የጥቃት ተግባር ነው"።

ለድቡብ እና ምስራቅ አፍሪካ ዓለም አቀፍ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ፖሊሲ ትብብር (CIPESA) ያደረገው ተጨማሪ ትንተና እንደሚያሳየው፣ ከፍተኛ የኦንላይን ጥቃት ስጋት ያለባቸው ሴቶች በህዝብ ዘንድ ታዋቂነት (public profile) ያላቸው ናቸው። ይህም ሴት ጋዜጠኞችን፣ ሴት የሰብአዊ መብት ተሟጋቾችን፣ የሴቶች መብት አክቲቪስቶችን፣ ወጣት ሴቶችን እና እንዲሁም ተደራራቢ ማንነቶች ስላሏቸው ተደራራቢ መድልዎ እና ጥቃት የሚደርስባቸውን ሴቶች ያጠቃልላል።



የ ቴክኖሎጂ አገዝ ጾታዊ ጥቃት ዓይነቶች

- **የአውታረ መረብ (ኦንላይን)ትንኮሳ፦** አንቺን ለማስፈራራት እና ለማድከም የሚላኩ ተከታታይ እና ኃይለኛ መልእክቶች።
- **የዝውውር ክትትል ፦** የት መገኘትሽን ወይም እንቅስቃሴሽን በዲጂታል መሣሪያዎች አማካኝነት በወቅቱ መከታተል።
- **በምስል ላይ የተመሰረተ ጥቃት ፦** ምስሎችሽን እንደ መሣሪያ በመጠቀም፣ በሰው ሰራሽ አስተውሎት (AI) የተቀነባበሩ የሀሰት ምስሎችን ጨምሮ አንቺን ለማሳፈር ወይም እንደ ቁስ ለመመልከት የሚፈጸም ጥቃት።
- **የግል መረጃን ማጋለጥ ፦** ለአካላዊ ጉዳት አሳልፎ ለመስጠት በማሰብ እንደ የመኖሪያ ቤት አድራሻሽ ወይም የስልክ ቁጥርሽ ያሉ የግል መረጃዎችሽን ያለፈቃድ ማውጣት
- **ዲጂታል ጾታዊ ጥቃት ፦** የመልእክት መለዋወጫ መተግበሪያዎችን ወይም ማህበራዊ ድረ-ገጾችን በመጠቀም ትንኮሳ መፈጸም፣ ማስገደድ ወይም ለጥቃት ማመቻቸት። ይህ ዓይነቱ ጥቃት ብዙ ጊዜ የሚፈጸመው ሴቶችን ለማሸማቀቅ እና እንዲደናገጡ ለማድረግ ነው።
- **ማጥመድ ፦** በዲጂታል ማታለያዎች ተጠቂዎችን ለአደገኛ አካላዊ ሁኔታዎች አሳልፎ መስጠት። ምንጮቹ እንደሚጠቁሙት፣ የኦንላይን ጥቃቶች ወደ አካላዊ አደጋ ሊሸጋገሩ ስለሚችሉ እንዲህ ያሉ የማታለያ ሙከራዎችን ነቅቶ መከታተል ያስፈልጋል።
- **ሰርጎ መግባት/ሀኪንግ ፦** መረጃ ለመስረቅ፣ ስምሽን ለማጥፋት ወይም የድርጅትሽን ስራ ለማስተጓጎል ያለ ህግ አግባብ ወደ አካውንቶችሽ (መለያዎችሽ) ሰርጎ መግባት።
- **የጥላቻ ንግግር፦** አድሏዊ ቃላትን/ቋንቋን መጠቀም በማንነትሽ ላይ የተመሰረተ ጥቃት መፈጸም።1

1 ብሮሹር፦ በቴክኖሎጂ የታገዘ በጾታ ላይ የተመሰረተ ጥቃት ምንድን ነው? በዩኤንኤፍፒኤ (UNFPA) የታተመ፣ መጋቢት 2023 እ.ኤ.አ።
ለምስራቅ እና ደቡብ አፍሪካ ዓለም አቀፍ የኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ (ICT) ፖሊሲ ትብብር (CIPESA) በአፍሪካ በሴቶች ላይ በሚደርስ የኦንላይን ጥቃት ዙሪያ ያደረገው ጥናት።

የተለመዱ የቴክኖሎጂ ተኮር የፆታ ጥቃት ዓይነቶች(በኢትዮጵያ)

በኢትዮጵያ፣ በቴክኖሎጂ የታገዘ መሰረተ ጾታ ጥቃት ብዙ ጊዜ ጥቅም ላይ የሚውለው ማህበራዊ፣ ባህላዊ እና ሃይማኖታዊ እሴቶችን እንደ መሣሪያ በመጠቀም ሴቶችን ዝም ለማሰኘት ነው። እነዚህ ጥቃቶች "በኢንተርኔት ላይ ብቻ" የሚቀሩ ሳይሆኑ፣ አንቺን ለማንቋሸሽ እና የውትወታ (advocacy) ስራሽን ለማቆም የታቀዱ እውነተኛ ስጋቶች ናቸው።

የጥቃት ዘዴ	ዝርዝር
የአውታረ መረብ (ኦንላይን) ትንኮሳ እና የጥላቻ ንግግር	በጾታ ላይ ያተኮሩ ስድቦችን፣ የአካል ማሸማቀቅን ወይም ሃይማኖታዊ ቃላትን በመጠቀም አንቺን "ስነ-ምግባር የሌላት" ወይም "ባህል አጥፊ" ብሎ መጥራት። ይህም አንቺን በማሸማቀቅ ዝም ለማሰኘት የሚደረግ ሙከራ ነው።
የጾታዊ ጥቃት እና የሞት ዛቻዎች	የአስገድዶ መድፈር፣ የአሲድ ጥቃት ወይም የሞት ዛቻ ያለባቸውን ግልጽ መልእክቶችን መላክ። ጥቃት አድራሾች አንቺን ለማስገደድ በልጆችሽ ወይም በቤተሰብ አባላትሽ ጭምር ዛቻ ሊሰነዝሩ ይችላሉ።
የግል መረጃን ማጋለጥ	የመኖሪያ ቤት አድራሻሽን፣ የስልክ ቁጥርሽን ወይም የሥራ ቦታሽን ያለፈቃድሽ ይፋ ማድረግ። ይህ የሚደረገው በአካል ክትትል እንዲደረግብሽ ወይም ጉዳት እንዲደርስብሽ ለማመቻቸት ነው።
ያለፈቃድ ምስል ማጋራት	አንቺን ለማዋረድ የግል ወይም የቅርብ ምስሎችን ማሰራጨት ወይም እናሰራጫለን በማለት ማስፈራራት። ይህ በሰው ሰራሽ አስተውሎት (AI) የተቀነባበሩ ወሲባዊ ምስሎችን (ማዘጋጀትንም ያካትታል።
መስሎ መቅረብ	(የሀሰት አካውንቶች)በመክፈት የአንቺን ምስሎች በመጠቀም የብሔር ጥላቻን ወይም "ሃይማኖት-ተቃዋሚ" አመለካከቶችን ማሰራጨት። ዓላማው በአንቺ ላይ ከባድ ማህበራዊ ወይም ፖለቲካዊ ግብረ-መልስ እንዲቀሰቀስ ማድረግ ነው።
የተቀነባበረ የሀሰት መረጃ	"ሰይጣኒስት"፣ "ሌዝቢያን" ወይም "የውጭ ወኪል" የሚሉ ታሪኮችን በአንቺ ላይ መለጠፍ። ማህበረሰቡ እውነት ነው በማለት እስኪያምኑ ድረስ እነዚህን ውሸቶች በቲክቶክ (TikTok) እና በቴሌግራም (Telegram) ላይ በተደጋጋሚ ያሰራጫሉ።
ሰርጎ መግባት እና ክትትል	የግል መልእክቶችሽን ለማንበብ ወደ አካውንቶችሽ ሰርጎ መግባት ወይም ስልክሽን መስረቅ። እንዲሁም የመብት ተሟጋችነት እንቅስቃሴሽን ለመቆጣጠር ጥሪዎችሽን እና ኢሜይሎችሽን መከታተልን ያካትታል።

በቴክኖሎጂ የታገዘ በጾታ ላይ የተመሰረተ ጥቃት የሚያሳድረው ተጽዕኖ፦ የማስጠንቀቂያ ምልክቶችን መለየት

በቴክኖሎጂ የታገዘ በጾታ ላይ የተመሰረተ ጥቃት ሴት አክቲቪስቶችን፣ ጋዜጠኞችን እና የሰብአዊ መብት ተሟጋቾችን በግልም ሆነ በሙያዊ ሕይወታቸው ላይ ያነጣጠረ ጥቃት ነው,።

ይህ ጥቃት ሆን ተብሎ የተነደፈው የአዕምሮ ጤናሽን ለመጉዳት፣ ስራሽን ለማስተጓጎል እና እውነተኛ (ከኢንተርኔት ውጭ ያሉ) የደህንነት ስጋቶችን ለመፍጠር ነው,። እነዚህን ተጽዕኖዎች አስቀድሞ መለየት አስፈላጊ የሆኑ የጥበቃ እርምጃዎችን ለመውሰድ ይረዳሻል።

የከአውታረ-መረብ (Online) ትንኮሳ የሚያሳድረው ተፅዕኖ

የጉዳት ዘርፍ	ምልክቶቹ
ስነ-ልቦናዊ ጉዳት	ከማያቋርጥ የኦንላይን ትንኮሳ የሚመነጭ የረጅም ጊዜ ጭንቀት፣ ፍርሃት፣ የአእምሮ መረበሽ (trauma) ወይም ከፍተኛ የስራ እና የህይወት መሰልቸት ።
ራስን መገደብ	ተጨማሪ ጥቃቶችን ለመሸሸግ በማሰብ ከዲጂታል ምህዳሩ ራሰን ለማግለል መገደድ፣ የማህበራዊ ሚዲያ አካውንቶችን ማጥፋት ወይም ድምጽን አጥፍቶ ለመቀመጥ መወሰን።
የስም ማጥፋት	በሀሰተኛ መረጃዎች ምክንያት በሰዎች ዘንድ ያለሽን አመኔታ ወይም ሙያዊ ተቀባይነት ማጣት፤ ይህም በስራሽ እና በሙያዊ ግንኙነቶችሽ ላይ እንቅፋት ይፈጥራል።
ራስን ማግለል	በፍርሃት ወይም በሀፍረት ምክንያት ከጓደኞችሽ፣ ከስራ ባልደረቦችሽ እና ከቅርብ ሰዎች ራስሽን ማግለል።
ከአውታረ-መረብ(On-line) ውጭ ያለ አደጋ	የonline ጥቃቱ ወደ አካላዊ ጥቃት ወይም በአንቺ፣ በቤትሽ እና በልጆችሽ ላይ ማደግ።

ይህ የዲጂታል ደህንነት እና አቅም ማጎልበቻ መመሪያ፣ ቴክኖሎጂ አገዝ ጾታዊ ጥቃቶችን ለመከላከል ግንባር ቀደም ሆነው ለሚሰሩ ሴቶች ታስቦ የተዘጋጀ ነው።

ምሳሌ፦ ጥቃቱ ከ(ኦንላይን) ወደ አካላዊ ትንኮሳ ሲሸጋገር

በኢትዮጵያ፣ የዲጂታል ጥቃት ብዙ ጊዜ አስከቶሎት የሚመጣ የመባባሻ መንገድ አለው። ይህንን ሂደት መረዳትሽ በአካላዊ አደጋ ውስጥ መሆንሽን ለመለየት ይረዳሻል።

በኢትዮጵያ ውስጥ ስለሴቶች መብት በኦንላይን የምትጽፍ አንዲት ፌሚኒስት አክቲቪስት፣ የጥቃት መልእክቶች ቢደርስዋት ጥቃቶቹም በሚከተለው መንገድ ሊባባሱ ይችላሉ፦

1. **የህዝብ ኢላማ ማድረግ ፦** ጥቃት አድራሾች በምትለጥፊያቸው ጽሁፎች ላይ የጥቃት ኮሜንቶችን በመጻፍ ይጀምራሉ።
2. **የታሪክ ጦርነት ፦** ማህበረሰቡ በአንቺ ላይ እንዲነሳሳ ለማድረግ የሀሰት አካውንቶች “ሃይማኖት-ተቃዋሚ”፣ “ሌዝቢያን” ፣ግብረ ሰዶም ወይም “የውጭ ወኪል” በማለት ውሸቶችን ያሰራጫሉ።
3. **የግላዊነት መጣስ ፦** አንድ ጥቃት አድራሽ የቤትሽን ፎቶ ይለጥፋል ወይም በየቀኑ በምትጓዥበት መንገድ ላይ አስተያየት ይሰጣል።
4. **ቤተሰብን ማስፈራራት ፦** ስለልጆችሽ ወይም ስለዘመዶችሽ የሚጠቅሱ እና “ዝም እንድትዪ” የሚጠነቅቁ መልእክቶች ይደርሱሻል።
5. **ቀጥተኛ ግንኙነት ፦** በኦንላይን የሚደርሱሽ ዛቻዎች በተመሳሳይ መልክ ማንነታቸው ባልታወቁ የስልክ ጥሪዎች ይደርሱሻል።

ማስጠንቀቂያ፦ እነዚህን ምልክቶች ካስተዋልሽ፣ የOnline ዛቻዎቹ ወደ አካላዊ እና ከአውታረ-መረብ(Off-line) ውጭ የሚከሰት አደጋ እየተሸጋገሩ መሆኑን ተረጂ።

ያልተመጣጠነ ጫና ፦ ሴቶች ብዙውን ጊዜ ትንኮሳን ዝም ብለው እንዲታገሱ ይጠበቅባቸዋል፤ ይህም ጉዳቱ ይበልጥ እንዲከብድ እና እንዳይታይ ያደርገዋል።

አስታውሺ፣ በዚህ ደረጃ ላይ አካላዊ ደህንነትሽ ዋነኛው እና አስቸኳይ ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ሊሆን ይገባል!

ቴክኖሎጂ ተኮር የፆታ ጥቃት ሲያጋጥመሽ ምን ማድረግ ትችያለሽ?

1

ማስረጃ አሰቀምጪ (ሁሉንም ሰነድ አድርጊ)

- ጥላቻ መልእክቶቹን ወዲያውኑ አታጥፊያቸው። ወደ ጠበቃ ወይም ፖሊስ የምትሄጂ ከሆነ እነዚህ መልእክቶች እንደ ማስረጃ ያስፈልጉሻል።
- እንዴት ማድረግ ይቻላል? የመልእክቶቹን፣ የጥቃት አድራሹን ፕሮፋይል (መገለጫ) እና የጥላቻ አስተያየቶቹን ፎቶ (screenshots) አንሺ።
- **ምን መካተት አለበት?** የምታነሺው ፎቶ ድርጊቱ የተፈጸመበትን ቀን እና ሰዓት ማሳየቱን እርግጠኛ ሁኚ። ግለሰቦች ስም ቢቀይሩ እንኳ ለማግኘት እንዲያስችል የፕሮፋይሎቹን ወይም የተለጠፉ መልዕክቶች ሊንኮች (URLs) መዝግበሽ አስቀምጪ።

2

አካውንቶችሽን (መለያዎችሽን) ጠብቂ

- ጥቃት እየደረሰብሽ ከሆነ፣ አካውንቶችሽን (መለያዎችሽን) በአስቸኳይ መጠበቅ አለብሽ።
- ባለ 12-ሆሄያት የይለፍ ቃል፦ የይለፍ ቃልሽን በጣም ረጅም ወደሆነ፣ ቢያንስ 12 ሆሄያት ወዳለው ቃል ቀይሪ። ትልልቅ እና ትንንሽ ፊደላትን፣ ቁጥሮችን እና እንደ (#፣ !፣ ወይም ?) ያሉ ልዩ ምልክቶችን ቀላቅለሽ ተጠቀሚ። ስምሽን ወይም የልደት ቀንሽን በፍጹም አትጠቀሚ።

ጠንካራ የይለፍ ቃል

- ከ12 በላይ ሆሄያት ሊኖሩት ይገባል፤ ይህም ትልልቅ እና ትንንሽ ፊደላትን፣ ምልክቶችን እና ቁጥሮችን ማካተት ይኖርበታል።
- ለእያንዳንዱ አካውንትሽ (መለያሽ) ልዩ እና የተለያየ መሆን አለበት።
- በግል መረጃዎች ላይ የተመሰረተ ወይም አንቺን በሚያውቁ ሰዎች በቀላሉ ሊገመት የሚችል መሆን የለበትም

ባለ ሁለት ደረጃ ማረጋገጫ (2FA) እንዴት መጠቀም ይቻላል?

1. ወደ አካውንትሽ የደህንነት ቅንብሮች (security settings) ግቢ።
2. ባለሁለት ደረጃ ማረጋገጫ (ወይም የመግቢያ ማረጋገጫ የሚለውን ፈልጊ አብሪው
3. አንዱን ዘዴ ምረጪ
4. በአጭር የጽሁፍ መልእክት የይለፍ ቁጥር ይደርስሻል።
5. የማረጋገጫ መተግበሪያ እንደ Google Authenticator ወይም Microsoft Authenticator ያሉ መተግበሪያዎችን ተጠቀሚ።
6. ከይለፍ ቃልሽ በኋላ፣ በገባሽ ቁጥር የሚላክልሽን የይለፍ ቃል አስገቢ
7. የማረጋገጫ መተግበሪያ (Authentication app)፦ እንደ Google Authenticator ወይም Microsoft Authenticator ያሉ መተግበሪያዎችን ተጠቀሚ።
8. ከይለፍ ቃልሽ በኋላ፣ በገባሽ ቁጥር የሚላክልሽን ኮድ አስገቢ

ጥቃት አድራሾቹን ዝም ማሰኘት (ሪፖርት እና ብሎክ ማድረግ)

- ጉዳት ሊያደርስብሽ የሚሞክርን ማንኛውንም ሰው የማገድ (ብሎክ የማድረግ) መብት አለሽ።

3

- ብሎክ :- ግለሰቦች ዳግመኛ መልእክት ቢልኩ ወይም የለቀቅሻቸውን ጽሁፎች ማየት እንዳይችሉ በፕሮፋይላቸዉ (መገለዎች) ላይ ያለውን “ብሎክ” የሚለውን ቁልፍ ተጠቀሚ።
- ለማህበራዊ ሚዲያው ሪፖርት አድርጊ:- ግለሰቦች ትንኮሳ እያደረሱብሽ መሆኑን ለፌስቡክ ፣ ለቲክቶክ ወይም ለቴሌግራም ለማመልከት “ሪፖርት” የሚለውን ቁልፍ ተጠቀሚ። አንቺን ከጥቃት የመጠበቅ የሁሉም ማህበራዊ ሚዲያ መድረክ ኃላፊነት ነው።

4

ብቸኛ አትሁኚ / እርዳታን ጠይቂ

- ጥቃት አድራሾች ብቸኝነት እንዲሰማሽ እና እንድትገለዪ ይፈልጋሉ። ያንን የዝምታ አጥር ለመስበር ለሌሎች ሰዎች ድምጽሽን አሰሚ።
- ለሌሎች ሰዎች አሳውቂ:- ለምትተማመኚባቸው ጓደኞችሽ፣ ለቤተሰብሽ ወይም ለሙያ ባልደረቦችሽ አማክሪ።
- ዲጂታል አጋርነትን ጠይቂ:- ጓደኞችሽ የ ዲጂታል ጥቃት የሚያደርሱብሽን አካውንት ሪፖርት በማድረግ እንዲረዱሽ ጠይቂያቸው። ብዙ ሰዎች በአንድ ጊዜ አንድን መለያ/አካውንት ሪፖርት ሲያደርጉ፣ የማህበራዊ ሚዲያ መድረኩ አካውንቱን የመዝጋት ወይም የማጥፋት ዕድሉ ከፍተኛ ይሆናል።

5

የቴክኖሎጂ ዕረፍት እረፍት መውሰድ

ዛቻዎቹን እየተቋቋምሽ ባለሽበት ወቅት ለጥቂት ግዜ ጽሁፎችን መለጠፍ ማቆም ወይም ፕሮፋይልሽን (መገለጫሽን) መደበቅ ምንም ችግር የለውም። እረፍት መውሰድ ማለት እጅ መስጠት ማለት አይደለም!

6

የህግ ከለላን ተጠቀሚ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (ኢፌዴሪ) ሕገ-መንግሥት መሰረት የኢንተርኔት ላይ ትንኮሳ ወንጀል ነው።

- የኮምፒውተር ወንጀል አዋጅ:- ይህ አዋጅ (አዋጅ ቁጥር 958/2016) ከኢንተርኔት ላይ ዛቻዎች እና ማንነትን ከመሰረቅ ይጠብቅሻል።
- የጥላቻ ንግግር እና የሀሰት መረጃ አዋጅ:- ይህ አዋጅ (አዋጅ ቁጥር 1185/2020) በጾታ ላይ ከተመሰረተ የጥላቻ ንግግር ጥበቃ ያደርግልሻል።
- ከባለሙያዎች ጋር መማከር:- ሪፖርት ለማቅረብ እንዲረዱሽ የድርጅትሽን የደህንነት ቡድን፣ ጠበቃ፣ ወይም በዲጂታል መብቶች ላይ የሚሰሩ የሰብአዊ መብት ድርጅቶችን አማክሪ።

የዲጂታል ደህንነት፦

የዲጂታል ደህንነት ማለት በስክሪን ፊት ስለምናሳልፈው ጊዜ ብቻ ማለት አይደለም፤ ይልቁንም ኢንተርኔቱ ሰላምሽን ወይም ዓላማሽን እንዳይሰርቅሽ ማረጋገጥ ነው። ጥቃት በሚሰነዘርብሽ ጊዜ፣ የመጀመሪያው ኢላማ አእምሮሽ ስለሆነ እራስሽን በተቻለ መልኩ መጠበቅ አለብሽ።

ዲጂታል ጫናን መለየት

የኢንተርኔት ላይ ጥቃት እንዲከብድሽ ተደርጎ የተነደፈ ነው ስለዚህ እነዚህን የማስጠንቀቂያ ምልክቶችን ተከታተዪ፦

- **ከፍተኛ ስጋት፦** አዳዲስ ጥቃቶችን ለማየት ስልክሽን ደጋግመሽ መፈተሽ ወይም ቀጣዩ ጥቃት መቼ ይሆን ብሎ መጠበቅ።
- **የብቸኝነት ወጥመድ ፦** ቤተሰቦችሽ ወይም ጓደኞችሽ ምላሻቸዉ ኢንተርኔት መጠቀም አቁሚ ብቻ ሊሆን ስለሚችል፣ ጉዳዩን ለእነሱ ማጋራት እንደማትችዪ ሆኖ መሰማት።
- **የሰውነት ምላሾች ፦** የማሳወቂያ ድምፅ (notification) በሰማሽ ቁጥር የልብ ምት መጨመር ወይም የሆድ መረበሽ ስሜት መሰማት።

ለአእምሮ ጤናሽ የሚረዱ እርምጃዎች/ መከላከያዎች

ሁከቱን/ጫጫታውን ለማስወገድ እነዚህን ዲጂታል ድንበሮች ተጠቀሚ፦

- **የማህበራዊ ሚዲያ ቦታዎችሽን ለይተሽ ተጠቀሚ፦** ከተቻለ ለስራሽ የተለየ፣ ከቤተሰብ እና ከጓደኞችሽ ጋር ለመገናኘት ደግሞ ሌላ የተለየ የማህበራዊ ሚዲያ አካውንት ተጠቀሚ። ይህም የሚደርስብሽን ጉዳት በአንድ ቦታ ብቻ በመገደብ ስሜታዊ ኃይልሽን ለመጠበቅ ይረዳሻል።
- **የተጣራ ይዘት፦** በአስተያየት መስጫዎች ውስጥ የተወሰኑ ቃላትን ወይም ስድቦችን ለመደበቅ የሚያስችሉ መሳሪያዎችን ተጠቀሚ።

በዩቲዩብ (YouTube)፣ በኤክስ (X) እና በኢንስታግራም (Instagram) ላይ፦ ወደ የግላዊነት ቅንብሮች ዉስጥ የታገዱ ቃላት በመግባት በአንቺ ላይ የሚሰነዘሩ ስድቦችን ወይም መጥፎ ስያሜዎችን ለምሳሌ “የውጭ ወኪል” ጨምሪ።

- **የምትከታተያቸውን ነገሮች ምረጪ፦** አንቺ ማለት የምታነቢው እና የምታየው ነገር ነሽ። ቁጣ እንዲሰማሽ ወይም የበታችነት እንዲሰማሽ የሚያደርጉ አካውንቶችን መከተል አቁሚ ። ይልቁንም ዲጂታል ደህንነታቸው የተጠበቁ ቦታዎችን እና ብርታት የሚሰጡሽን ሌሎች ሴቶችን ተከተዪ።
- **የ”ጀምበር” (Sunset) ህግ፦** አእምሮሽ በሰላም ለመተኛት እንዲችል ከዲጂታሉ ዓለም ጫና ለመረጋጋት ጊዜ ያስፈልገዋል። ስለዚህም ከሁለት ሰዓት በፊት ስራ ነክ የሆኑ አካውንቶችን መፈተሽ አቁሚ።

የሚከተለው ዝርዝር እንደ ዲጂታል ደህንነት ያገለግላል። በወሩ የመጀመሪያ ቀን በስልክሽ ላይ ማስታወሻ በመሙላት እነዚህን ምርመራ አከናዉኚ።

ልምድ	መወሰድ ያለበት እርምጃ	
ዲካዎችሽን አጽጂ	ላለፉት 3 ወራት ያልተጠቀምሽባቸውን መተግበሪያዎች (apps) አጥፊ። ወደ ስልክሽ የመተግበሪያ ፈቃዶች በመግባት ለማያስፈልጉ መተግበሪያዎች የካሜራ እና የቦታ አገልግሎቶችን ዝጊ።	
መግቢያዎችሽን አጽጂ	በፌስቡክ፣ በቴሌግራም እና በጂሜይል ላይ ወደ ደህንነት ክፍል ግቢ። የገቡ መሣሪያዎች የሚለውን ተመልከቺ። የማታውቂው ስልክ ወይም ከተማ ካየሽ ወዲያውኑ “Log Out” /መውጫ(የሚለውን ተጫኚ።	☐
የሶፍትዌር ጥገና	በስልክሽ እና በላፕቶፕሽ ላይ የሶፍትዌር ማሻሻያ መኖሩን ፈትሺ። እነዚህ ማሻሻያዎች ሰርጎ ገቦች ወደ መሣሪያሽ ለመግባት የሚጠቀሙባቸውን ቀዳዳዎች የሚደፍኑ ናቸው።	☐

ልምድ	መወሰድ ያለበት እርምጃ	
ከለላሽን ፈትሺ	ቪፒኤንሽን (እንደ ProtonVPN ያሉ) ከፍተሽ አሁንም እየሰራ መሆኑን አረጋግጪ። የይለፍ ቃል መቆጣጠሪያሽ ተተኪ መረጃ መያዙን እና ዋናውን የይለፍ ቃልሽን ማስታወስሽን አረጋግጪ።	☐
የጎግል ቴስት	ጎግል ላይ የራስሽን ስም እና የስልክ ቁጥር ፈልጊ። የቤት አድራሻሽን ወይም የግል መረጃሽን ካገኘሽ፣ ጎግል መረጃውን እንዲያጠፋው(ሪፖርት) የሚለውን መሣሪያ ተጠቀሚ።	☐



በጉዞ ላይ የሚጸረጉ የጸህንነት ጥንቃቄዎች – የህዝብ ዋይፋይን እንጻ ከፍተኛ ሰጋት ተመልከቺ

ጥንቃቄ የሚሹ ተግባራትን አስወግጂ

በካፌዎች ወይም በአውሮፕላን ማረፊያዎች ውስጥ ኢንተርኔት መጠቀም አደገኛ ሊሆን ይችላል፤ ምክንያቱም እነዚህ ኔትወርኮች ብዙውን ጊዜ ያልተመሰጠሩ (unencrypted) ናቸው።



ወጥመዲ

ሰርጎ ገቦች የአንቺን የኢንተርኔት እንቅስቃሴ ለማየት እንዲችሉ፣ እንደ “ነፃ ኢንተርኔት” ያለ ማራኪ ስም በመስጠት የሐሰት ዋይ ፋይ በመፍጠር ሊያታልሉሽ ይችላሉ።

መፍትሄው



ካላስፈለገሽ በስተቀር ነፃ ኢንተርኔት አትጠቀሚ፣ይልቁንም የራስሽን የሞባይል ዳታ ተጠቀሚ።



የግድ መጠቀም ካለብሽ በመጀመሪያ ቪፒኤን (VPN) አብሪ ይህም በመረጃዎ ዙሪያ ደህንነቱ የተጠበቀ መተላለፊያ ይፈጥራል።



ጥንቃቄ የሚሹ ተግባራትን አስወግጂ በህዝብ ዋይ ፋይ ላይ እያለሽ በፍፁም ወደ ባንክ አካውንትሽ አትግቢ ወይም ሚስጥራዊ የሆኑ የንቅናቄ (activ-ist)ሰነዶችን አትላኪ።

ቪፒኤን እንዴት ጥቅም ላይ ይውላል?

1. **አስተማማኝ ቪፒኤን ምረጪ**
   (ለምሳሌ፦ ProtonVPN ወይም Windscribe)። እነዚህ መተግበሪያዎች ነፃ ወይም በክፍያ የሚገኙ ስሪቶች አሏቸው።
2. **የቪፒኤን መተግበሪያውን በመሣሪያሽ ላይ ጭኚ**
   መተግበሪያውን አውርደሽ በስልክሽ ወይም በላፕቶፕሽ ላይ መጫን ይኖርብሻል።
3. **መተግበሪያውን ከፈቺ እና ሰርቨር ምረጪ**
   መተግበሪያውን ከፈተሽ በኋላ የራስሽን ሀገር ወይም በአቅራቢያ ያለ ሀገር ሰርቨር ምረጪ።

ማሳሰቢያ፦ ኢንተርኔት መጠቀም ከመጀመርሽ በፊት ሁልጊዜ ቪፒኤኑን ማብራትሽን አረጋግጪ



ዲጂታል አጋርነት፦ እርስ በርሳችን የጸህንነት ጋሻዎች ነን

ጂታል አጋርነት ማለት ሴቶች የኦንላይን ጥቃትን ብቻቸውን እንዲጋፈጡ አለመፍቀድ ማለት ነው። ጥቃት አድራሾች ኃይል የሚያገኙት ከእኛ ዝምታ ሲሆን፣ ብዙውን ጊዜ ተጎጂዎቻቸውን ነጥሎ ለማጥቃት ይሞክራሉ። ቴክኖሎጂ አገዝ ጾታዊ ጥቃቶችን ለመከላከል በግንባር ቀደምትነት ለሚሰሩ ሴቶች አብሮ መቆም ይህንን የብቸኝነት ስሜት የሚቀንስ ሲሆን፣ ማንኛውንም ጥቃት ብቻውን የምትጋፈጥ ሴት አለመኖርዋን ያሳያል።

በቅርብ ጊዜ በተከሰቱ የ"ጄን ዚ" ንቅናቄዎች ወቅት፣ በብዙ አገሮች የሚገኙ ወጣት አክቲቪስቶች መረጃን በፍጥነት ለመለዋወጥ፣ እርስ በርስ ለመደጋገፍ እና የጋራ እርምጃዎችን ለማስተባበር ማህበራዊ ሚዲያዎችን በመጠቀም ለዲጂታል ጭቆናዎች የጋራ ምላሽ ሰጥተዋል፣ ተሳታፊዎችን ለመጠበቅ እና ግንዛቤን ለማስፋት የሚረዳ የጋራ ዓላማም ፈጥረዋል።

አንዲት እህት በቴክኖሎጂ የታገዘ በጾታ ላይ የተመሰረተ ጥቃት ሰለባ መሆኗን ስታዪ፣ ዝም ብለሽ አትለፊ፤ እርምጃ ውሰጂ!

እርምጃ	ምን ማድረግ ትችያለሽ?
ጥቃቱን በግልጽ መቃወም	ድርጊቱ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ለማሳየት ትንኮሳውን ወይም ጥቃት አድራሾቹን በግልጽ መቃወም።
የጋራ ሪፖርት ማድረግ	ግለሰቧ የተለጠፈባትን ምስል/ፅሁፍ ብዙ ሰዎች በአንድ ጊዜ ሪፖርት እንዲያደርጉ በማስተባበር ከማህበራዊ ሚዲያ ገጾች (ፌስቡክ፣ ቲክቶክ ወዘተ) እንዲወገድ ማድረግ።
መረጃዎችን ማጋራት	እንደ ጥላ አይነቶች የደህንነት መመሪያዎች፣ ማስጠንቀቂያዎች እና መሣሪያዎች ለሌሎች ሴቶች ማድረስ እና ሌሎች ሴቶች ራሳቸውን እንዲጠብቁ መርዳት
ድምጿን ማስተጋባት	የተጎጂዋ ድምፅ በጥቃት አድራሾች ጫጫታ እንዳይዋጥ መልእክቷን ወይም ሥራዋን ለሌሎች ማጋራት።
ፈጣን ምላሽ መስጠት	አስቸኳይ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ ፈጣን ድጋፍ ለመስጠት እና መረጃዎችን ለማጋራት ከጓደኞችሽ እና ከሥራ ባልደረቦችሽ ጋር መተባበር።

በግንባር ቀደምትነት ለሚሰሩ ሴቶች የጋራ ምላሽ መስጠት ጥቃት አድራሾችን ተስፋ ያስቆርጣል። ስለሆነም ትክክለኛ መረጃ እንዲሰራጭ፣እንዲሁም ዛቻዎች በግልጽ እንዲታዩ እና ማስረጃ እንዲያዝባቸው ማድረግ ደህንነትን ይጨምራል። በጋራ በመንቀሳቀስ የሥልጣን ሚዛኑን ከጥቃት አድራሾች ወደ ተጎጂዎች በመመለስ ሴቶች ሥራቸውን በራስ መተማመን እንዲቀጥሉ ይረዳል።

በቴክኖሎጂ የታገዘ ፆታዊ ተኮር ጥቃት እንደ ተራ ነገር ሊታይ አይገባም፤ ሴቶች ኢንተርኔት ስለተጠቀሙ ብቻ የሚመጣ ተግዳሮት አድርገው ሊቀበሉት አይገባም። ይህ በጋራ ትግል እና በአጋርነት ሊመከት የሚገባ የሰብአዊ መብት ጉዳይ ነው።

በፌሚኒስት ግኝት፣ በጾታ ላይ የተመሰረተ ጥቃት ስር መሰረቱ የወንድ የበላይነት የሥልጣን መዋቅር ሲሆን፣ ይህንን በጋራ መቃወም ራስን የማብቃት አንዱ ተግባር ነው።

መከላከል ጥንካሬ ሲሆን፣ጥበቃ ማድረግ ፖለቲካዊ ውሳኔ ነው!

xilla

Afaan Oromo

XILAA (DIBAABEE)

Nagummaa Dijitaalaa fi Meeshaalee of-eeggannoo dandamachiisoo Dubartoota Adda dureedhaan Haleellaa Saalaa Teknooloojiidhaan Deggeramee Raawwatu(TFGBV) Qolachuuf hojjetaniif.

Waa'ee Addis Paawor Haawus(Addis Powerhouse)

AddisPaawor Haawusiin(APH) dhaabbata feeministii wiirtuu oomisha beekumsaa fi falma mirga dubartootaa dubartoota dargaggootaan hogganamu ta'ee dubartoota Itoophiyaa keessa jiran qu'annoodhaan, barnoota dijitaalaatiin, fi diriilee miidiyaa barbaachisoo ta'an hidhachiisuudhaan rakkoolee moggeessuu hawwaasummaaf Siyaasaa, akkasumas Aggaammii Koorniyaa qiyyaafate dura dhaabbachuuf of-kennuudhaan hojjetuudha.

Dhaabbanni keenya bara 20220, wayita uggura kooviid-19-yeroo itti rakkoon garaa garummaa saalaa hawaasa dinagdee fi sirna siyaasaa keessatti hammaatee mul'atetti, akkasumas haalli jireenya hawaasummaa fi hojii saffisaan gara dirree Oonlaayiniitti jijjiirame keessatti hundeeffame.

Wayita ce'umsaa kanaatti, ragaan(data) koorniyaa looge, odeeffannoon sobaa bal'inaan akka faca'ee fi Aggaammiin Saala irratti xiyyeeffate mudachuu irra darbee dubartoota gama oonlaayinii fi ooflaayiniitiin hammam akka moggaatti dhiibe argine. Yaadowwan dhalatan kunneen duula hubannoo babal'isuu falmii dhimma mirgaa qorannoo irratti xiyyeeffatee fi tarsiimawaa ta'een, sagaleewwan moggaatti dhiibaman gara beekumsa, warraaqsaa fi dhiibbaa sirna qabeessaatti jijjiiru hojiirra akka oolchinuuf kaka'umsa nuuf ta'an. Yeroo hundeeffama keenyaa irraa qabee, gareen Addis Paawor Haawus(APH), hojii qorannowwan garaa garaa geggeessuu, duula sagalee dhageessisuu, dookimentaroota seenessaa hedduu qopheessuudhaan, kunis Itoophiyaa keessatti sagalee dubartootaa ol-kaasuu irratti sadarkaa biyyoolessaatti poodacaastii feeministii isa jalqabaa isa taasisa.

Dubbii Dursaa(Foreword)

Yeroo Addis Powerhouse hundeessinu, nageenya dubartoota fuulduratti argaman tiksuun dirqama akka ta'e hubanne.

Wayita Dirreen hawwaasummaa Itoophiyaa saffisaan dhiphachaa dhufe kana keessatti, bakka hordoffiin(to'annoon), odeeffannoo sobaa fi weeraroonni qindaa'aan meeshaalee afaan cufsiisuu ta'anii itti fayyadamaman keessatti, nageenyi keenya ammas filannoo miti — haal-duree dirqama ta'e kan sochii activiizimii keenyaati.

Guuboon meeshaalee Xilaa, jecha Afaan Amaaraa kan "dibaabee" jedhu irraa fudhatamuudhaan dubartoota aadda duree ta'an haleellaa dijitaalaa, doorsisaa fi aggaammii haleellaa hojii isaanii irratti afaan isaan cufsiisuuf raawwatu irraa akka gaachanaatti isaan golguuf bakka bu'a.

Nuti Dibaabee (Xilaa) kan uumne nageenya keessanii fi sagalee keessan keessa tokko filachuun akka isinirraa hin eegamneefi.

Jabinni warraaqsa keenyaa hammuma jabina dubartoota warraaqsicha hoggananii qofa akka ta'e ammanna. Daangaa dijitaala keessanii eeggachuudhaafi sagaleen keessan ol-ka'ee akka dhagaa'amuuf qabeenyota kanatti fayyadamaa!

Garee APH
Amajjii 2026

Haleellaan Saalaa Tekinooloojiidhaan Deggeramee Raawwatu (TFGBV) Maali?



